## I የሥራ ሂደቱ አገልግሎቶችና ዝርዝር አፈፃፀም

በቀጥታ ለተገልጋዩ የሚሰጡ አገልግሎቶች

1. ማህበራት ማደራጀት
2. የንግድ ስራ አመራር ስልጠና
3. የንግድ ልማት ምክር አገልግሎት
4. የኤክስቴንሽን ልማት ሥራዎች

   በኮንስትራክሽን ስራ
   በብረታ ብረትና እንጨት ስራ፣
   በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣
   ምግብ ማቀነባበርና የከተማ ግብርና

5. የአጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠና
6. የመሥሪያና መሸጫ ቤትና ቦታ አቅርቦት
7. የብድር አቅርቦት ማመቻቸት
8. የማምረቻ መሣሪያና ተስማሚ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ማመቻቸት
9. የገበያ ድጋፍ አገልግሎት ማመቻቸት

ጎንለጎን የሚከናወኑ ተግባራት

1. ደንብ፣ መመሪያና ማኑዋል ማዘጋጀት
2. ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈፃፀሙን መከታተል
3. መረጃ ማሰባሰብና ትንታኔ ማድረግ
4. የቅስቀሳ ስራ መስራት
5. የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት
6. የንግድ ሥራ አመራር ስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት
7. የማምረቻና መሸጫ ቦታ አቅርቦት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
8. የብድር አቅርቦት ፈንድ ጥናት ማዘጋጀት
9. የተስማሚ ቴክኖሎጂ ጥናትና ልማት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
10. የገበያ ድጋፍ ማድረግ

## የአገልግሎቶች ዝርዝር አፈፃፀም

ለተገልጋዩ በቀጥታ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር አፈፃፀም

1. ማህበራት ማደራጀት

   በማህበር ተደራጅቶ ለመስራት ፍላጎቱ ያላቸው ተጠቃሚዎችን ምዝገባ ማካሄድ

   ስለ ማህበር አደረጃጀት አስፈላጊነትና ስለጠቀሜታው ለተገልጋዮች ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ ማስጨበጥ

   እንደ ስራ መስኩና ክህሎታቸው መመልመልና ምዝገባ ማካሄድ

   የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ አዘጋጅተው እንዲያፀድቁ እና የማህበር የሥራ አመራር አባላትና ንዑሣን ኮሚቴዎችን እንዲመርጡ ማገዝ

   የሚያንቀሳቅሱበትን ቢዝነስ የንግድ ስራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

   የማህበር ማደራጃ ሠነዶች የተሟሉ ስለመሆናቸው ማጣራት እና ሕጋዊ ሠውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

   ለኢንተርፕራይዞች የግንባታ ደረጃ ፈቃድና አመታዊ ዕድሳት እንዲሰጣቸው የድጋፍ ደብዳቤ

   ለከተሞች ዲዛይንና ኮንስትራክሽን የሥራ ሂደት መፃፍ፤

2. የንግድ ስራ አመራር ስልጠናና መስጠት

   በየስራ መስኩ የሰልጠና ፍላጎት መለየት

   የስልጠና ተሳ ዎችን ለይቶ መመዝገብ

   በሚከተሉት ርዕሶች ስልጠና መስጠት

   - በንግድዎን ይጀምሩ፣
   - በኢንተርፐርነርሺፕ፣
   - በገበያ አያያዝና መረጃ፣
   - በወጪ ስሌትና የዋጋ ትመና፣
   - በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣
   - በንግድ ሥራ ዕቅድ አዘገጃጀት፣
   - በሴቶች የንግድ ብቃት ማበልፀጊያ፣
   - በንግድ ስራ አስተዳደር፣
   - በመሠረታዊ የንግድ ክህሎት፣
   - በአዋጭ የንግድ ሃሳብ ማመንጨት፣
   - የሴፈ ስልጠና መስጠት ፣

   በሥል ና ፣ የተገኘውን እርካታ መለኪያ መጠይቅ በማስሞላት አፈነናሙን መ ም ም

   ለሠልጣኞች የሥልጠና ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

## 3. የንግድ ልማት ምክር አገልግሎት

የንግድ ልማት ምክር አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መመልመልና መመዝገብ

ከንግድ ልማት ምክር አገልግሎት ተጠቃሚው ጋር በመወያየት ስምምነት መፍጠር

የሁኔታዎች ትንተና እና የጋራ የድርጊት ፕሮግራም በኢንተርፕራይዙ ባለቤትና በምክር ሰጪው ባለሙያ እንዲዘጋጅ ማድረግ

በድርጊት ፕሮግራሙ መሠረት የንግድ ልማት ምክር አገልግሎቱን መስጠት እና አፈጻፀሙን መገምገም

በተለያዩ ምክንያቶች በማኀበራት አባላት መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የማስማማት ሥራ መስራት

## 4. የኤክስቴንሺን ልማት አገልግሎት

### 4.1 በኮንስትራክሽን ስራ

በየጥሬ ዕቃ መረጣ፣ አጠቃምና አያያዝ ምክር መስጠት

በፕሪካስት ቢም፣ የብሎኬት፣ ጡብ፣ ጠጠር፣ የወለልና ግድግዳ ንጣፍ ምርት አመራረት ሂደት እና የእያንዳንዱን ውህደት ጥምርታ በተግባር ማሳየት

ምርቱ ከተመረተ በኂላ ለአገልግሎት እሰከሚውል ድረሰ ሊኖር በሚችለው የቆይታ ጊዜና አያያዝ ምክር መስጠት

በተመረቱ ምርቶች ደረጃ፣ ጥራት አጠባበቅና አያያዝ ትምህርትና ግንዛቤ መስጠት

በብሎኬት፣ በፕሪካስት ማምረቻ፣ በጠጠር መፍጫ መሣሪያዎችን አጠቃቀምና አያያዝ በተግባር ማሳያት፣

የኢንተርፕራይዙን ሁኔታዊ ትንተና መርሐ -ግብር በማዘጋጀት የምክር አገልግሎት መስጠት፣

### 4.2 በብረታ ብረትና እንጨት ስራ፣

አምራች ኢንተርፕራይዝ ዲዛይን አንብበው መስራት እንዲችሉ ድጋፍ መስጠት፣

በጥሬ ዕቃ መረጣ፣ አጠቃቀምና አያያዝ ምክር መስጠት፣

የብረታብረት እና እንጨት አቆራረጥ፣ አበያየድ፣ አገጣጠም፣ አለሳለስ፣ አስተሻሸግና ቅብ ስራ በተመለከተ በተግባር ማሳየትና መደገፍ፣

በተመረቱ ምርቶች ጥራት አጠባበቅ፣ አስተሻሸግና አያያዝ ትምህርትና ግንዛቤ መስጠት፣

የማምረቻ መሣሪያና ተስማሚ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አያያዝ በተግባር ማሳያት፣

4.3 በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣

በጥሬ ዕቃ መረጣ፣ አጠቃቀምና አያያዝ ምክር መስጠት፣

አምራች ኢንተርፕራይዞች ዲዛይን አንብበው ጨርቅ፣ ቆዳ መቁረጥ፣ መስፋት፣ ቁልፍ መትከል፣ መዘምመዘም፣ መተኮስ፣ ማተምና ማቅለም በተመለከተ በተግባር ማሳየትና መደገፍ፣

በባህላዊ የሚሸመኑ ልብሶች የተለያዩ ዲዛይኖችን አሰራር ማሳየት፣

በተመረቱ ምርቶች ጥራት አጠባበቅ፣ አስተሻሸግና አያያዝ ትምህርትና ግንዛቤ መስጠት፣

የሽመና ማምረቻ መሣሪያዎች እና የልብስ ስፌት ማሽኖችን አጠቃቀምና አያያዝ በተግባር ማሳያት፣

4.4 ምግብ ማቀነባበርና የከተማ ግብርና

በጥሬ ዕቃ መረጣ፣ አጠቃቀምና አያያዝ ምክር መስጠት፣

በደረቅ ምግብ፣ በወተት፣ በማር፣ ቅመማቅመም ውህደትና አስተሻሸግ በተግባር ማሳየት፣

የተመረቱ ምርቶች ደረጃ፣ ጥራት፣ የቆይታ ጊዜ፣ አጠባበቅና አያያዝ ትምህርትና ግንዛቤ መስጠት፣

በመፍጫ፣ መናጫ፣ መጨመቂያ፣ ማቡኪያ፣ መጋገሪያ፣ ማቀዝቀዣና ማሸጊያ ማሽን አጠቃቀምና አያያዝ በተግባር ማሳያት፣

5. የአጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲሰጥ ድጋፍ ማድረግ

በፓኬጅ የሥራ መስኮች  ስራ ለሚጀምሩ ሠልጣኞች ፍላጎተ ስልጠና መለየት፣ መመዝገብ እና ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋም መላክ፣

በየክላስተሩ የገቡ ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን  የክህሎት  ክፍተት በመለየት ወደ ቴክኒክና ሙያ  ተቋም መላክ፣

6. የመሥሪያና መሸጫ ቤትና  ቦታ  አቅርቦት

በየከተማው ለኢንተርፕራይዞች ልማት አገልግሎት የሚውል  በማስተር ፕላን ወይም ዕድገት ፕላን የተደገፈ እና መሠረተ ልማት የተሟላለት የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ከመሬትና መሠረተ ልማት ዝግጅት፣ አቅርቦትና አስተዳደር የስራ ሂደት መረከብ፤

ለክፍት የገበያ ማዕከላት፣ ለተንቀሳቃሽ  ሱቆች እና  ለእሁድ ገበያዎች የሚሆኑ ቦታዎችን ተለይቶ  መዘጋጀቱን መከታተልና ማረጋገጥ፣

የመስሪና መሸጫ ቤት ፍላጎት ጥያቄ መቀበልና በክላስተር፣ የሚገቡትን በቅደም ተከተል በመለየት ምዝገባ ማካሄድ፣

የማህበር አባላት በማህበራቸው ስም የማምረቻ ቤት በውሉ መሠረት እንዲረከቡ የድጋፍ ደብዳቤ መስጠትና አፈፃፀሙን መከታተል፣

7. የብድር አቅርቦት አገልግሎት

ተዘጋጅቶ የቀረበውን ቢዝነስ ፕላን መርምሮ እና አስተካክሎ በመስሪያ ቦታው በአካል ተገኝቶ ትክክለኛነቱን በመገምገም ማጽደቅ፣

ለብድር የቀረቡ ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆናቸው በማጣራት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ማስተላለፍ፣

ስለ ብድር አወሳሰድ፣ አጠቃቀምና የቁጠባ ባህል በግንባር ስልጠናና ምክር አገልግሎት መስጠት፣

የተሰራጨውን ብድር በወቅቱ እንዲሰበሰብ ድጋፍ መስጠት፣

በተዘጋጀው የማምረቻ መሣሪያ ዝርዝር መግለጫ /Specification/ መሠረት መግባባት ላይ ለመድረስ ከኢንተርፕራይዝ ማህበር አባላት ጋር መወያየት፣

ስለ ማምረቻ መሣሪያው አጠቃቀምና አያያዝ የምክር አገልግሎት መስጠት፣

የማምረቻ መሣሪያዎቹ ሊዝ ወይም ኪራይ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲሰበሰብ ድጋፍ መስጠት፣

8. የገበያ ድጋፍ አገልግሎት

ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ለይቶ ማወቅና መመዝገብ፣

ለሚመረቱ ምርቶች አስፈላጊ የሆኑ የጥሬ ዕቃ ምንጮች መለየትና መረጃ መስጠት፣

የሚመረቱ ምርቶች በንግድ ትርዒት፣ በባዛር፣ ማስተዋወቅ የማስተባበር ስራ መስራት፣

የገበያ ትስስር መፍጠር፣

ጎንለጎን የሚከናወኑ ተግባራት ዝርዝር አፈፃፀም

1. ደንብ፣ መመሪያና ማኑዋል ማዘጋጀት፣ ጥናቶችን ማድረግ

በተለያዩ ርዕሶች ጥናቶችን ማካሄድ
የሥልጠና ማንዋሎችን ማዘጋጀት
የሚሻሻሉ ደንብና መመሪያዎችን በመለየት ረቂቅ ማዘጋጀት
የተዘጋጀ ጥናቶች፣ ማንዋሎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ረቂቅ በማቅረብ ማስተቸትና ማፀደቅ
የጸደቁ ማኑዋሎችና መመሪያዎቹ ማሳተምና ማሰራጨት
ለኢንተርፕራይዞች ልማት ግብዓት አቅራቢ ተቋማት ሊመሩበት የሚያስችል ደንብ፣ መመሪያ፣ መስፈርቶች ማዘጋጀት

2. ቅት ማዘ ትና አፈ ናሙን መከታተል

ለ ቅት ፀት የሚ ስፈል · መረ ችን መሰበሰብ፣ ማደራጀትና ዓመታዊ ቅት ማዘ ት
በ ቅ ላ መ የትና ማጽደቅ
ቅ ን በየሩብ ዓመቱ መከፋፈልና አፈፃፀሙን መከታተል
የክንውን ሪፖርት ማዘ ትና ማቅረብ
የተከናወኑ ተግባራትን በግንባር ተገኝቶ መገምገም
ግብረ-መልስ ማዘጋጀትና መስጠት

3. መረጃ ማሰባሰብና ትንታኔ ማድረግና ማሰራጨት

6. የማምረቻና መሸጫ ቦታ አቅርቦት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

መሠረተ ልማት የተሟላለትና በሳይት ፕላን የተደገፈ የመሥሪያና የመሸጫ ቦታ እንዲረከቡ ማድረግ

ለክላስተር ማዕከላት የሚሆኑ ቤቶች ዲዛይን ማሰራት

በገበያ ላይ ውሱንነት ያላቸውን የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎች በብቃት እንዲገኝ ማመቻቸት

ወጪ ቆጣቢና ዘመናዊ የሆኑ የግንባታ ዘዴዎችንና ማቴሪያሎችን በማጥናትና በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
የክላስተር ግንባታና ለግንባታው የሚያስፈልጉ ማቴርያሎች አቀራረብ ላይ ክትትል ማድረግ፣

የመስሪያና መሸጫ ቤት ተጠቃሚዎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ በአዲስ ገቢዎች የሚተኩበትን አግባብ ተከታትሎመፈፀም

የተረከቡትን የማምረቻና የመሸጫ ቦታና ቤት በአግባቡ ስለመጠቀማቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

7. የብድር አቅርቦት ፈንድ ጥናት ማዘጋጀት

ለኢንተርፕራይዞች ልማት ለተገልጋዮች ስለሚቀርብ ብድር በተመለተ ከአቅራቢው ድርጅት ጋር በጋራ የደንብ መሻሻያ ስራ መስራት

የብድር አገልግሎቱ በቀጥታ በአንድ ማዕከል ውስጥ የሚሰጥበት አግባብ እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸት

የብድር ፍላጎት መረጃ ማሰባሰብ

መረጃውን ማደራጀት፣ መተንተንና ሠነድ ማዘጋጀት

የተዘጋጀውን የብድር ፍላጎት ጥናት ሠነድ ማቅረብ

በጥናቱ መሠረት ለብድር አገልግሎት የሚውል ፈንድ ማሰባሰብ

የተገኘውን የብድር ፈንድ ለተገልጋዮች እንዲደርስ ለአበዳሪው ተቋም እና ለየከተሞቹ ዝርዝር መረጃውን ማስተላለፍ

የተገኘውን የብድር ፈንድ ከነምንጩ ለአበዳሪው ተቋም በማሳወቅ አግባብ ያለው ስርጭት እንዲያካሂድ ድጋፍ ማድረግ

በአበዳሪው ተቋም በኩል ብድሩ በአግባቡ ስለመሰራጨቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

የማምረቻ መሣሪያዎች ፍላጎት በየሥራ መስኩ እና ተገልጋዮች ብዛት መለየትና መመዝገብ

በግሉ ዘርፍ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የሚስፋፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

በአበዳሪው ተቋም በኩል የጨረታ ሠነድ ተዘጋጅቶ ማስታወቂያ መውጣቱን ክትትል ማድረግ

የኢንተርፕራይዞች ብድር አቅርቦት፣ ስርጨትና አመላለስን በተመለከተ በየጊዝው የክትትልና ድጋፍ ሥራ መሥራት፣

ተገዝተው የቀረቡ ማምረቻ መሣሪያዎች በወጣው ዝርዝር መግለጫ መሠረት መሆናቸውን ማረጋገጥና ርክክብ እንዲፈፀም ማድረግ

**8.** የተስማሚ ቴክኖሎጂ ጥናትና ልማት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

በተስማሚ ቴክኖሎጂ ጥናት፣ ልማት እና አጫጭር የሙያ ማሻሻያ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት የሚችልበት አደረጃጃትና አቅም መፍጠር

ለኢንተርፕራይዞች ልማት የሚውሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች መረጃ ማሰባሰብ (ለኮንስትራክሽን፣ እንጨትና ብረታብረት፣ ምግብ ማቀነባበር፣ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የከተማ ግብርና )

በኮንስትራክሽን፣ እንጨትና ብረታብረት፣ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ምግብ ማቀነባበር እና የምርት ማሽጊያ ዲዛይንና ሞዴል አፈላልጎ ማግኘት እና መመዝገብ

የዲዛይኖችን ተስማሚነት ማረጋገጥና የዲዛይን ማስተካከያ ማድረግ

በዲዛኑ መሠረት ተስማሚ ቴኬኖሎጂ ሞዴል መሰራቱን ማረጋገጥ

ለተመረተው ተስማሚ ቴክኖሎጂ ጥራት ማረጋገጫ እንዲሰጥ ማመቻቸት፣

ጥራታቸው የተረጋገጡ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና ማስተዋወቅ

በተሰራጩ ቴክኖሎጂዎች ላይ አስፈላጊውን አስተያየት ከተጠቃሚዎች በማሰባሰብ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ

በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ኢንተርፕራይዞች መካከል የምርት ጥራት ውድድር በማድረግ አሸናፊዎችን መለየትና ግብረመልስ መስጠት

ለኤክስቴንሽን ኤጀንቶች የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሥራት፣

አዳዲስ ለሚመረቱ ቴክኖሎጂዎች ስለአመራረቱና ስለ አጠቃቀሙ ማንዋሎችን ማዘጋጀት

የማምረቻ መሣሪያዎችን ስፔሲፊኬሽን በየሥራ መስኩ ለይቶ ማዘጋጀት

ኢንተርፕራይዞች ለሚገለገሉባቸው ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችና የማምረቻ መሣሪዎች የጥገና አገልግሎትና የመለዋወጫ መሣሪያ እንዲያገኙ የማመቻቸት ስራ መሥራት

ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የቴክኖሎጂና የምርት ግብዓት ቁርኝት እንዲኖራቸው ማመቻቸት፣

9. የገበያ ድጋፍ ማድረግ

ኢንተርፕራይዞች ለሚያመርቷቸው ምርቶች በቂ ገበያ ስለመፈጠሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ለይቶ ማወቅና መመዝገብ

በኢንተርፕራይዞች ለሚመረቱ ምርቶችና አገልግሎቶች የገበያ ፍላጎት መረጃ መሰብሰብና ማወቅ

በኢንተርፕራይዞች የሚመረቱ ምርቶች የሀገር ውስጥና የአለም ዓቀፍ የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉ ስለ መሆናቸው ለማረጋገጥ የምርት ናሙና በመላክ ማስመርመር

ለኤክስፖርት የሚመረቱ ምርቶች፣ መለየትና ድጋፍ መስጠት

## በቀጥታ ለተገልጋዩ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ማህበራትን ለማደራጀት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች

   በማህበር ለመራጀት ፍላጎቱ ያላቸው አምስትና ከዚያ በለይ የሆኑ ፈቃደኛ ሠዎች፣

   የአባልነት ማመልከቻ የተሞላበት ቅጽ፣

   የአባላት የከተማ ነዋሪነት ማስረጃ፣

   በፓኬጅ ለሚደራጁ የትምህርት ማስረጃና የስራ ልምድ ካለ፣

   የማህበር መመስረቻ ቃለ ጉባዔ፣

   በአባላት የተፈረመ የማህበር መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ፣

2. የሥራ አመራር ስልጠና ለመስጠት የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች

   የሥልጠና ፍላጎት ማመልከቻ ጥያቄ፣

   ተለይቶ የቀረበ ፍላጎተ ስልጠና፣

   የሥልጠና ወጪ ለመጋራት ፈቃደኛ የሆነ፣

3. የአጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠና

   የሥልጠና ፍላጎት ማመልከቻ ጥያቄ፣

   ተለይቶ የቀረበ ፍላጎተ ስልጠና/የክህሎት ክፍተት/፣

   ለስልጠናው ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ፣

   የሥልጠና ወጪ ለመጋራት ፈቃደኛ የሆነ፣

4. የንግድ ልማት ምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ

   የምክር አገልግሎቱን ለማግኘት ፍላጎት ያለው ስለመሆኑ የተሞላ ፎርም፣

   አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁ ወጪዎችን ለመጋራት ፈቃደኛ የሆነ፣

5. የማምረቻና መሸጫ ቦታና ቤት አቅርቦት ቅድመ ሁኔታ

የማምረቻና መሸጫ ቤት ጥያቄ፣

በማህበር ለተደራጁ የህጋዊ ሠውነት ማራጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

ቀደም ሲል የማምረቻና መሸጫ ቦታና ቤት ያልወሰዱ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ለማስፋፊያ ቦታ የሚጠይቁ ቀደም ሲል የወሰዱትን ቦታና ቤት በአግባቡ ስለመጠቀማቸው ማስረጃ፣

የንግድ ስራ እቅድ፣

6. የብድር አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ

የብድር ፍላጎት ጥያቄ ማመልከቻ፣

ግለሰብ ተበዳሪዎች ከሚኖሩበት ክፍለ ከተማ የመኖሪያ ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ለማህበራት የህጋዊ ሠውነት ማራጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

የንግድ ስራ ዕቅድ፣

የብድር ዋስትና፣

ቀደም ሲል ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ ማስረጃ፣

7. የገበያ ድጋፍ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ

ለማህበራት የህጋዊ ሠውነት ማራጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

በግል የገበያ ድጋፍ ለሚጠይቁ በስራ ሂደቱ በተመረጡ የስራ መስክ የተሰማሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ፣

በኮንስትራክሽን እና ዲዛይን ሥራ ለተሰማሩ እና ለሚሰማሩ ለኮነስትራክሽን ሥራ የተሰጠ የሥራ ደረጃ ፈቃድ፣

ተቋሙ ምርቱንና አገልግሎቱን ለመሸጥ ያለው ብቃትና የጥራት ማረጋገጫ (እንደአስፈላጊነቱ)፣

8. የማምረቻ መሣሪያና ተስማሚ ቴክኖሎጂ አቅርቦት

የማምረቻ መሣሪያና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ፍላጎት ጥያቄ፣

ለማህበራት የህጋዊ ሠውነት ማራጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

የማምረቻ መሣሪያው ዓይነት ዝርዝር መግለጫ (Specification)